# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
# 8 ኛ ሳምንት
# ከእግዚአብሔር ጋር መታገል

## ዓላማ

❖ በፀሎት ስለመጽናት መማር፣

## የሚጠና ጥቅስ

❖ «ለምኑ ይሰጣችኋል፣ፈልጉ ታገኙኛላችሁ፣መዝጊያንም አንኳኩ ይከፈትላችሁማል፡፡» ሉቃ.11÷9-13 ፣

## ተጨማሪ ምንባባት

❖ ዘፍጥረት 32÷22-32፣ሉቃ18÷1-8፣11÷9-13

## መግቢያ፣

❖ ከልብ የፈለጋችሁትን ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ አይሆንም ስትባሉ ጥያቄውን ታቆማላችሁ? እንዲያውም እውነተኛ ፍላጐታችን ሲሆን እስኪፈጸምልን ደጋግመን እንጠይቃለን፡፡የማያቋርጥ ጥያቄ ታቀርባላችሁ፣ጸሎታችንም ያለማቋረጥ በትጋት መሆን አለበት፡፡እግዚአብሔርም ወዲያው ይመልስልናል፡፡

❖ ቢሠጠን የሚጐዳንና የማይጠቅመን ሲሆን ፡፡ወዲያው የማናገኝበትም ግዜ አለ፡፡ጸሎታችንን ካላቋረጥን መሻታችንን አያስቀርብንም፣ በዛሬው ትምህርታችንም የይስሀቅ ልጀ ያዕቆብ በትጋት የተቀበለውን በረከት እናያለን፡፡

## ትምህርቱ፣

❖ ያዕቆብ የይስሀቅ ልጅ የአብርሃም የልጅ ልጅ ነው፡፡ ለቤተሰቡም ታዛዥ ነበር፡፡ እናቱ ርብቃም ከወንድሙ ከኤሳው ይልቅ እርሱን ትወደው ነበር፡፡ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን በረከት ምንነት ያውቅ ነበር፡፡

❖ በብሉይኪዳን የበኩር ልጅ የልዩ በረከቶች ባለመብት ነበር፡፡ ከኤሳውና ያዕቆብ የብኩርና በረከትን የመቀበል መብት የነበረው ማን እንደነበር ታስታውሳለችሁ ?

❖ ከወጣትነቱ ጀምሮ ያዕቆብ የአባቱን ቡራኬ ይፈለግ ነበር፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቡራኬ በአባቱ በኩል እንደሚያልፍ ያውቅ ነበር፡፡ በታቃራኒው ኤሳው የብኩርና በረከቱን አላከበራትም ለያዕቆብ ሸጠለት፣ ያዕቆብም ከአባቱ ተቀበላት፡፡

❖ በኋላ ሕይወቱም ያዕቆብ ወደ ከነአን ሲመለስ፣ ከአጐቱ ቤት ቤተሰቡን ይዞ ሲመለስ፣ ሌሊቱን ከአንድ ሰው ጋር ሲታገል አደረ፡፡ ሰውየውም ተወኝ ልሂድ አለው፡፡ ያዕቆብ ግን ***«ካልባረከኝ አለቅህም»*** ዘፍ. 32÷26፣ አለው፡፡ ሰውየውም ባረከው ስሙንም ከያዕቆብ ወደ እስራኤል ቀየረው፡፡ ሲነጋም ለመባረክ የታገለው እግዚአብሔር እንደ ነበር ተረዳ፡፡

❖ ስለዚህም ያዕቆብ የአብርሃም የይስሀቅን በረከት ወረሰ፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳንም በእርሱ ተፈፀመ፡፡ የታላቅ ሀገርና ሕዝብ የእስራኤል አባት ሆነ- እስራኤል - ሕዝበ እግዚአብሔር ማለት ነውና፡፡

## ማጠቃለያ፣

### ከእግዚአብሔር የመባረክ ጥቅም

❖ የእግዚአብሔርን በረከት መሻት አስፈላጊ ነው፡፡ ከያዕቆብ ታሪክ እንደምናየው በይስሀቅ የእግዚብሔርን በረከት ተቀብሎዋል፡፡ ስለዚህ በቤተሰቦቻችን የምንመረቀው ምርቃት የእግዚአብሔር በረከት ነው፡፡

- ❖ እግዚአብሔር በሐዲስኪዳን በርካታ የበረከት ምክንያቶችን ሰጥቶናል፡፡ስናስቀድስ እንባረካለን፡፡ ስንቆርብ እንባረካለን፣ በወንጌልና ቅዱሳት መጻሕፍት፣ በመስቀል፣ በካህናት፣ በጳጳሳት እና ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች /አባቶች/ ሁሉ እንባረካለን፡፡ እግዚአብሔር እንድንባረክ ይሄን ሁሉ ሰጥቶናል፡፡

<u>ወደ እግዚብሔር ስንጸልይ የመጽናት አስፈላጊነት/ጥቅም/</u>

- ❖ በትጋት ካላማቋረጥ መጸለይ ለጸሎታችን መልስ ለማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡
- ❖ ሳይታክቱ የመጸለይ ጥቅም ጌታችን የመበለቲቱን ምሳሌ ሲጠቅስ ተገልጾልናል ሉቃ. 18÷1-8 በዚህም መበለቲቱ ለአንድ አመጸኛ ዳኛ ይፈርድላት ዘንድ አብዝታ ስለወተወተችው፡፡ ከባላጋራዋ ፈርዶላታል፡፡ ***«እንኪያስ እግዚአብሔር÷ ቀንና ለሊት ወደ እርሱ ለሚጮሁ ለሚታገሳቸውም ምርጦቹ አይፈረድላቸውምን?»***
- ❖ ጌታችን በሎቃ.11÷11-13 እንደተናገረው ወላጆች ለልጆች የተሻለውን እንደሚያደርጉ እግዚአብሔርም የሚበልጠውን ይሠጠናል፡፡

<u>ያዕቆብ ቁሳቁስ ላይ አላተኮረም፥ በእግዚአብሔር በረከት ላይ አተኰረ እንጂ</u>፡፡

❖የእግዚአብሔርን በረከት ከፈለግን በሕይወታችን የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሠጠናል፡፡ሰሎሞን እግዚአብሔርን የጠየቀውን ታስታውሳላችሁ?.... የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ጥበብን ጠየቀ ገንዘብ ወይም ቁሳዊ ነገር አልጠየቀምና እግዚአብሔር ጥበብንና ያልጠየቀውንም ሀብት ሰጠው፡፡

<u>ጥያቄ፣</u>

1. ያያዕቆብን ታሪክ በየትኛው የመጽሐፍ-ቅዱስ ክፍል ታገኙታላችሁ?
2. ኤሳው ብኩርናውንና የአባቱን በረከት እንዴት አጣ?
3. ወደ ቤተክርስቲያን ስትመጡ የምትቀበሉትን በረከት ታስባላችሁ? ቤተክርስቲያን በመምጣት ለመባረክ በምን ትሳተፋላችሁ?
4. እግዚአብሔር ለአብርሃም እና ለይስሀቅ የገባላቸው ቃል ኪዳን ምን ነበር?
5. ከወላጆቻችሁና ከአያቶቻችሁ በረከትን ትቀበላላችሁ? ከማንኛቸውም የተቀበላችሁትን የቡራኬ ቃላት ፃፉ፣
6. እግዚአብሔርም ምን እንደምትፈልጉ ቢጠይቃችሁ ምን ትጠይቁታላችሁ?

**ይቆየን፡፡**